# ከዋናው መሥሪያ ቤት የመጣው እንግዳ

## ክፍል ፫

ከበልጅግ አሊ

የጉመሮ ሻይ ተክል ከቀኑ ሃሳብና ድካም ለመገላገል የቸኮለ ይመስል የጨለማውን ብርድ ልብስ ተገን በማድረግ አሸልቦል።ከሩቅ የሚሰማው የኤሌትሪክ ማመንጫ ሞተር የጉመሮን ፀጥታ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ ያደፈርሰዋል።ሞተሩ ሲጠፋ የሾፌሩ ገብረመድህን ውሻና የግምጃ ቤቱ ሰራተኛ ጥላሁን ድመት ጠባቸውን በመቀጠል ቦታውን ይወስዳሉ።በወቅቱ ድርቅ ምክንያት እንቁራሪቶቹ ውሃው ጥም ሰለበዛባቸው ጩኸታቸው ከመቸውም የበለጠ ጎልቶ ይሰማል። የፌንጣዎቹ ጩኸት ከእንቁራሪቶቹ ጋር ፉክክር የያዙ ይመስላል። የጥላሁን ድመት ከገብረመድህን ውሻ ጋር ጠቡ ሲሰለቻት የቤቱን በር በጥፍሯ ፍቃ ታስከፍትና ገብታ እግር ስር ተጠቅልላ ትተኛለች።ድመቷ ከገባች በኋላ ውሻው ጠቡ መቆሙ ያሳዘነው ይመስል አለፍ አለፍ እያለ ያላዝናል።አንዳንዴም በየአካባቢው የሚራወጡትን የማታ ነፍሳት እየተመለከተ ይጮኻል።አብዛኛው ሠራተኛ ከዋናው መስሪያ ቤት የመጣው እንግዳ ሻይ ልማቱ እንዲዘጋ ሪፖርት ያቀርባል ተብሎ ስለተወራ እንቅልፉን አጥቶ ይህንን የተደበላለቀ ጩኸት እንደ አዲስ ሙዚቃ በዚህ ሌሊት ያዳምጣል።

ከዋናው መስሪያ ቤት የመጣው እንግዳ አቶ አስፋው የመጣበትን አዲስ የሩስያ መኪና ድሎት ሲያማርር ቆይቶ ስለድርቁ ምንም ሳያወራ ወደ እንግዳ መቀበያ ቤት ሂዷዋል። የእንግዳ መቀበያው ቤት የተሰራው በከፍተኛ ቦታ ስለሆነ እዚያ ሆኖ መላው የሻይ ተክሉን መመልከት ይቻላል። አብዮቱ ፈንድቶ ሻይ ልማቱ ከመወረሱ በፊት ባለቤት የነበረው ፈረንጅ እዚህ ቤት ውስጥ በመቀመጥ ሁሉንም ሠራተኛ የሩቅን አቅርቦ በሚያሳይ መነፅር ይቆጣጠር ነበር።ይህንን ዓይነት አገልግሎት የሚሰጥ ዘመናዊ መሣሪያ መኖሩን የማያውቁ የሻይ ተክሉ ሠራተኞች በሥራ በሚያለምጡበት ግዜ ፈረንጁ ስለሚያውቅባቸው ይገረሙም ነበር። እርስ በእርስም የሚነግረው አለ ብለው ጥርጥር ውስጥ ገብተው ነበር።

የእንግዳ መቀበያው ቤት አሰራሩ በአውሮፓውያን ቤት አሰራር አይነት ሲሆን ውስጡም ዘመናዊ በሚባሉ ቁሳቁሶች የተሟላ ነው። የገላ መታጠቢያውና ሽንት ቤቶቹም ሁሉ እንደ ጉመሮ ባለ ሩቅ ቦታ ይገኛሉ ብሎ ለማመን ያዳግታል። ይህን የእንግዳ ቤት ንፅህናው የሚጠብቀውና እንግዳ ሲመጣ ምግብ የሚያቀርበው የፈረንጁ ወጥ ቤት የነበረው ተካ ነው።ተካ መጀመሪያ የተቀጠረው በፈረንጁ ጊዜ ሲሆን የተለያዩ ምግቦችን በመስራት የታወቀ ነው። እዚህ ማረፊያ ቤት የመጡ ሁሉ አቶ አስፋውን ሳይጨምር ያደንቁታል።ተካ ደግና ሰውን ማስተናገድ የሚወድ ሲሆን አቶ አስፋውን መቀበል ግን ምንግዜም ቢሆን ደስታ አይሰጠውም።

አቶ አስፋው እንግዳ መቀበያ ቤት ሲደርስ ተካ ከወጥ ቤት ውስጥ ወጥቶ በአንገቱ አጥልቆ ባሸረጠው ጨርቅ ላይ እጆቹን እየጠራረገ ለሰላምታ አንገቱን ጎንበስ ቀና እያደረገ ከመኪናው ውስጥ ሻንጣውን አውጥቶ አቶ አስፋው የሚወደው ክፍል ውስጥ አስገብቶ ወደ ወጥ ቤት ተመለሰ። አቶ አስፋው በመንገድ የደከመውን ሰውነቱን ዘና ለማድረግ ገላውን ታጥቦ ተካ ያቀረበለትን ተመግቦ እንደተለመደው የሃሮል ሮቢንስንን መፅሐፍ ከመደርደሪያው አውርዶ እያነበበ በዛው እንቅልፍ ይዞት ሄደ።ለእርሱ የቀኑ ፍፃሜ ሲሆን በዚህ ሌሊት የጉመሮ ሰራተኞች እንቅልፍ አጥተው ነበር ።

-፪-

እሮብ ገበያ ጉመሮ ሲተኛ ደግሞ በተራዋ ከእንቅልፏ ተነስታለች።እሮብ ገበያ እንደ ሌሊት ወፍ ቀን ቀን ተኝታ ማታ ማታ ትነቃለች ።ማታ እንደተለመደው ጠጅ ቤቶቿ ይሞላሉ። ነዋሪዎቿ ከሥራ ወጥተው ወደ ቤት ይገባሉ። ልጆች ከትምህርት ቤት ይመለሳሉ። የእሮብ ገበያ ሕይወት መንቀሳቀስ ይጀምራል።በዛሬው ምሽት አቶ አስፋው ሰለመጣ ምን አልባት የሚናፈሰውን ወሬ ለመስማት በጉመሮ ሠራተኞች ከተማዋ ከወትሮው ይልቅ ሞልታለች።

ገረመው እንደተለመደው እመሃል ተቀምጦ ገቢው ወጭውን አዲስ ዜና አለኝ በሚል ፈገግታ ግብዣቸውን እንደሚጠብቅ በማመልከት የሚገቡትን ሁሉ ሰላምታ እየሰጠ ይቀበላል። ሊቁ መሃል ከገረመው ጎን ተቀምጦ ራዲዮኑን ጆሮው ስር ገትሮ ያዳምጣል። ራዲዮኑ አዲስ የደርግ አዋጅ ስለሚተላለፍ ምን እንደሆነ አጥርቶ ለመስማት ቢከብደውም እየታገለ ያዳምጣል።

አባ እሸቱ ገና ምንም ስላልቀመሱ ጢማቸውን እያሻሹ ሊቁን እየተመለከቱ በአንክሮ ምን አዲስ ነገር እንደለ ይጠይቁታል። ሊቁም ምን አዲስ ነገር አለ ብለው ሁልግዜ አዋጅ ነው። አዋጅን በአዋጅ መሻር ነው ። ለአንዱ አዋጅ ስንደንስ ለሌላው እናገለድማለን ። ለአንዱ አዋጅ ሙሾ ስንደረድር ፣ለሌላው ከበሮ እናነሳለን። ተዋክበው ያዋክቡናል እንጂ ምን አዲስ ነገር ይኖራል ብሎ መለሰላቸው።

እውነትህን ነው ልጄ ሕይወታችን በሰው እጅ አይደለች ምን ይደረግ ብለህ? በሕይወታችን ማዘዝ ከአቆምን በኃላ እኮ ነው ፍርሃት የዋጠን። ለእኛ ህይወት እናስባለን ። ለልጆቻችንን ህይወት እናስባለን። ለማናዝበት ህይወታችን ማሰባችን ምን ያህል አድካሚ መሰለህ? እንግዲህ ቀኑ ደርሷል ። አልነቃችሁም ፣ አልተደራጃችሁም፣ አልታጠቃችሁም ብለው እህል ወሃችንን እናቋርጠዋለን ብለው እንግዲ ጥርቅም ያድርጉት እንጂ በማናዝበት ህይወታችን ብንቃወምስ እሷንስ እናጣት የል? ብለው ሰሞኑን ከሌላኛው አስተማሪ ጋር ያደረጉትን ክርክር አጣቅሰው የእንግዳው መምጣት እንዳሳሰባቸው ተናግረው ጠጃቸውን አንስተው ቀመሱ።

አባ እሸቱ አለ ሊቁ ፊቱ ሲታይ ይህቺን ሰዓት በጉጉት ይጠብቃት ይመስል በሰው እጅ የተያዘች ህይወት እኮ አንድ ቀን ከያዛት ልታመልጥ ትችላለች።ሁል ግዜ እንደተያዘች አትኖርም።መጥፎው ተስፋ መቁረጥ ነው። መብትን ለማግኘት እስከምትነቁ ፣ እስከምትደራጁ ፣ እስከምትታጠቁ ጠብቁ ማለት አይቻልም። ወይም ደግሞ የነቃ፣ የተደራጀ፣ የታጠቀ ህዝብ ዝም ብለው የሚመሩት አህያ መሆን የለበትም። ንቃት ለባርነት ከሆነ ባፍንጫችን ይውጣ ብሎ እሱም ጠጁን ቀመሰ።

አሂሂ አሉ አባ እሸቱ ጨዋታው እየደመቀ የሰው ዓይንና ጆሮ ወደ እሳቸው መሆኑ ስለታወቃቸው እየተደሰቱ ዘና ብለው ታዲያ ለዛ ለአስተማሪው የስራ ባልደረባህ አትነግረውም ። ሎጂክ ፣ሎጂክ እያለ በማናውቀው እንግሊዝተኛ ቋንቋ ሲነተርከን ለሰነበተው ። ምን ይዞህ ነበር አፍህን የዘጋህ? ልጄ የአንተም ህይወት በሱ እጇ ስላለች አይደል? አንተም መልስ ለመስጠት የፈራኸው። የልጆችህ ነፍስ ደግሞ በአንተ እጅ ሆና አሳሰበችህ። እንደ ድሮው ጎረምሳ ብንሆን፣ የምናስተዳድረው ባይኖርማ እናሳይህ ነበር።

ሊቁ ቀና ብሎ ራዲዮኑን አጠፋፍቶ ተስተካክሎ አባ እሸቱን መመልከት ሲጀምር ሁሉም ሰው ጸጥ ብሎ ማዳመጥ ጀመረ። ይስሙኝ አባቴ ልብ ይበሉ ነግሬዎት የማላውቀውን ነገር ልንገሮት ። ሁላችሁም አዳምጡኝ በሚል አስተያየት አይኑን በማጉረጥረጥ በጠጅ ቤት ውስጥ ያለውን ሁሉ ቃኘ። እውነትም ሰው ሁሉ ይህ ስውር መልእክት የገባው ይመስል እሱን ማየት ጀመሩ።



EthioLion.com

እዚህ ሃገር መጀመሪያ ስመጣ ከመቃብር ውስጥ አምልጬ ነው የመጣሁት። በእዚች አለም ላይ የሚጠብቀኝ ቢኖር ሞት ብቻ እንደነበረ ዘወትር የማልረሳው የቀን ቅዠቴ ነው። ምድር ከድታኝ ፣ ሃገሬ አላውቅህም ብላኝ። የሚያውቀኝ ያየኝ ሰው ሁሉ እኔን በማየቱ ብቻ ሞት እንደሚፈረድበት እየመሰለው ትንፋሽ ሲያጥረው ፣ እኔ ጥላዬን ስፈራ ፣ ጥላዬ እኔን ሲፈራ፣ ህይወቴ ከእኔም ከሰውም ቁጥጥር ውስጥ ወጥታ ከመንግስተ ሰማያትና ከገሃነብ እሳት የት እንደምገባ በማስብበት ወቅት ነበር። እሬሳን እንደ ድንጋይ ተሸጋግሬ ፣ በደም ውስጥ ዋኝቼ ፣ የነፍስ ሲቃ ይዞኝ ፣ የምሄድበትንም ሳላውቅ ፣ እግሬ ወደ መራኝ ተጉዤ ነው እዚህ የመጣሁት። እዚህ ስመጣም እንደቤተሰብ ምንነቴን ሳትጠይቁኝ ወዳችሁኝ የተቀበላችሁኝን አሁን ችግር ውስጥ ብትገቡ ፈርቼ የምተዋችሁ፣ ከእናንተ የምሸሽ ይመስላችኃል? ፍርሃት ምንድነው አባ እሸቱ?

ፈራህ ይበሉኝ አባ እሸቱ? ምኑን ነው የምፈራው አባቴ ? በቁሜ ከሞትኩ በኋላ ፣ መርዶዬ ለቤተሰቤ ተነግሮ ተዝካሬ ከወጣ ፣ ስሜ ተለውጦ ሌላ ስም ከያዝኩ በኋላ፡ እኔ ማንነቴን ክጄ ፣ እራሴን ደብቄ ስለኖርኩ ፣ በየቀኑ እንደ ድኩላ በሃገሬ እየተሳቀቅሁ ስለምኖር ፣ ይህም ኑሮ ተብሎ ነው ፍርሃት ሕይወቴን የሚያሰቃያት? አባ እሸቱ ተሳስተዋል እኔ የምፈራው ነገር የለም። የምፈራው ነገር ቢኖር እራሴን ብቻ ነው ። እራሴን እንዳላጠፋ ብዬ እንጂ የምጠነቀቀው። ይህ እዚህ ግባ የማይሉት ጥራዝ ነጠቅ አዋቂ ነኝ ባይ ጋግርታም የምርት ካድሬ እኔን በምንም በምንም ሊያስፈራራኝ አይችልም ። ከዚህ በታች የትም ሊያሳንሰኝ ስለማይችል አልፈራም ብሎ አይኑን እያጉረጠረጠ አባ እሸቱን ማየት ጀመረ።

ገረመው የአባ እሸቱና የሊቁ ጉዳይ እንዳይካረር በማሰብ ወሬው ለመቀየር ያህል ያ ሆዳም ገና ከመምጣቱ የተካን ምግብ ለመለቃቀም ወደ እንግዳ ቤት እየሮጠ ሄደኮ በማለት ጨዋታውን ወደ አቶ አስፋው በመቀየሩ ለሁሉም ሰው እፎይታን ሰጠው። የጠጅ ቤቱ ወሬ ግሎ ሁሉም በየፊናው በአቶ አስፋው ላይ ስድቡን፣እርግማኑንና ሽሙጡን ሲያወርድበት መሸ።

አባ እሸቱም ከሊቁ ጋር እንደገና ጨዋታ ጀምረው።ልጄ የአንተ ጀግንነት እኮ አይነ ውኃህ ላይ ተፅፎል። ሁለተኛው ፎቶህ ከእኛ ጋር እንደሚኖርና ፣ አንደኛውን ፎቶህን ግን ለመግደል የምታደርገውን ጥረት የማንገነዘበው ከመሰለህ ተሳስተሃል። ቀን ሲያልፍ አንደኛውን ፎቶህን እናውቀው ይሆናል። አሁን ግን በንዴት ተነሳስተህ ይህንን መናገርህ ማለፊያ ጉዳይ አይደለም። ልጃችን ነህና ማሰባችን አይቀርም ። ብዙዎቻችንን ግፋ ቢል ጎሬ ነው ብለን የመጣን አይደለንም? ብዙም አትከብደንም አሉት።ሊቁን ከገባበት የኃዘን የንዴትና የሃሳብ ጉዞ ለመመለስም ፣ለማፅናናትም በሚሞክር ደግነት በተቀላቀለበት አባታዊ ዓይኖቻቸው ዐይኖቹን እየፈለጉ።ብዙው የጉመሮ ሠራተኛ ይህንን “ ግፋ ቢል ጎሬ ነው“ የሚለው አነጋገር ስለማይጥመው ፀጥታ ሰፈነ። አባ እሸቱ “ ግፋ ቢል ጎሬ ነው “ የሚለውን አባባል ያነሱት ከተለያዩ የኢትዮጵያ አውራጃዎችና ክፍለ ሃገሮች ግለሰቦች ጥፋት፣ ወንጀል ሰርተው በመንግስት ሲፈለጉ አማራጭ ያለው ጎሬ መምጣት ነበር።ምክንያቱም ጎሬ ሩቅ ስለሆነ ባለስልጣን እዚህ ድረስ መጥቶ አይፈልጋቸውም። ስራም ደግሞ አገሩ የቡና አገር ስለሆነ በቀላል ይገኛል።ብዙዎቹ ሠራተኞች ወደ ትውልድ ስፍራቸው አይሄዱምም ነበር።

ሊቁ ከዛ በላይ ጠልቆ መግባት አልፈለገም ። ገረመው እንግዳው መጥቶ እንግዳ ቤት እንዳረፈና ሁሉም በጉጉት ስለሚጠብቀው የሻይ ተክሉ የወደፊት እጣ ምንም እንዳልተነፈሰ ሃዘኔታ በተሞላበት ሁኔታ ራሱን እየነቀነቀ ከተናገረ በኋላ የዕለቱን የአዲስ ዜና አቅራቢነት ሥራ የጨረሰ ይመስል የተረፈውን ጠጅ ጨልጦ ቀስ ብሎ ብድግ አለ። የገረመው ከመቀመጫው

መነሳት የውይይቱ ማብቂያ ደውል ይመስል ሁሉም የሱን ፈለግ መከተል ጀመሩ። ሊቁም ከጠጅ ቤቱ ሲወጣ እንደተለመደው እየጮኸ ፤ የሞትኩ መርዶዬ የተበላ ነኝ፣ አንድ ሞት አደለም መቶ ሞት አምልጫለሁ፣ ደም የሰው ደም ተሻግሬ የመጣሁ ነኝ ፣ አጥንት በጥይት ተነድሎ ያየሁ ነኝ፣ የሰው ሰጋ ሲጠበስ የሸተተኝ ፣ ሲል ቆየና ዜማውን ወደ ዘፈን ቀየር አደርጎ

እባክሽ ቁንጫ ገላሽን ታጠቢ፣ፀጉርሽን ተሰሪ
አምላክ ካደረገሽ የኔ አስተዳዳሪ።

እያለ ወደ ቤቱ ሄደ።

ምሽቱ ተለውጦ ንጋት ሲሆን ጉመሮ በሌላ ጩኸት ተተካ ። የጥላሁን ድመትና የገብረመድህን ውሻ ጩኸታቸው አይሰማም። ፌንጣዎችና እንቁራሪቶች ጮኸታቸውን ያቁሙ አያቁሙ የሚውቅ የለም ግን የሚሰማቸውም የለም። የካቦው የይስማው አውራ ዶሮ ቦታውን ከገብረመድህን ውሻ ወሰደ። የናስር ትራክተር ሻይ ለቃሚዎችን በየቦታው ለማድረስ ከማን አንሼ በሚል ማጓራቱን ቀጠለ። ታደሰ የኤሌትሪኩ ሠራተኛ „ „እንደምን አደራችሁ። እግዝሄር ለየሰው እንደስራው ለዕፅዋቱና ለእንስሳቱ ዝነብላቸው“ እያለ የጠዋት ፆሎቱን በጩኸት ማስተጋባት ቀጠለ። የሠራተኞቹ ልጆች ከሊቁ ጋር ሊውሉ ከየቤታቸውና ከየጎጃቸው እየወጡ ቀስ በቀስ በቡድን በቡድን እየተከማቹ ወደ ትምህርት ቤት አመሩ ።

ከዋናው መስሪያ ቤት የመጣው እንግዳ ተካ የሰራለትን ቁርስ በረንዳው ላይ ሆኖ መመገብ ጀመረ።ቁርሱን በልቶ ሲያበቃ እንደተለመደው ካኪ ሱሪና ፣ ካኪ ሸሚዙን ነጭ ባርሜጣውን አድርጎ ትላንት ስድብ ሲያወርድባት በነበረችው መኪና ቁልቁል ወደ ቢሮ የሚወስደውን መንገድ ተያያዘው። በየሻይ ተክሉ ውስጥ በስራ የተሰማራው ሠራተኛ ሁሉ ከመኪናዋ ጋር ሃሳቡ ቁልቁል ወረደ።

ቢሮ ሲደርስ መልከ መልካሙና የጥቁር ቆንጆ ብለው የዕሮብ ገበያ አዝማሪዎች የሚዘፍኑለት የጉመሮ ሻይ ልማት ሥራ አስኪያጅ አቶ ማሞ ከቢሮው ወጥቶ ተቀበለው። አቶ አስፋውና አቶ ማሞ የሚተዋወቁት እዚህ ሳይሆን በከፋ ክፍለ ሃገር በሚገኘው ውሽውሽ ሻይ ልማት ውስጥ ነው። አቶ አስፋው አቶ ማሞን በቂ ባልሆነ ምክንያት ከውሽውሽ ስራ አስኪያጅነት አውርዶ ተራ የክፍል አላፊ አድርጎት ነበር።በኋላም ከፀጉሩ ብዛትና ከሰውነቱ ቅጥነት የተነሳ የተፋ እስኪርቢቶ የፃፈው አንድ ቁጥር የሚስለው የጉመሮ የቀድሞ ሥራ አስኪያጅ ወደ አዲስ አበባ ሲቀየር አቶ ማሞ እድል አግኝቶ ከውሽውሽ ተቀይሮ ፣ በአቶ ወርቁ የዋናው መስሪያ ቤት ሥራ አስኪያጅ ተሹሞ ነው ወደ ጉመሮ የመጣው። አቶ አስፋው የዋናውን ስራ አስኪያጅ ትዕዛዝ ማጠፍ ስለማይችል አቶ ማሞን ከመጣላት ወዳጅ አደረገው። አቶ ማሞም ውሽውሽ ሻይ ልማት የደረሰበትን ስቃይ ላለመድገም የሩቅ ወዳጅነትን ተቀብሎ አቶ አስፋው የሚወደውን እያደረገ ተከባብረው መሥራት ጀመሩ።

ቢሮ ገብተው ትንሽ ከቆዩ በኋላ እየተቁነጠነጠ የተቃጠለውን ሻይ አሳዩኝ ብሎ አቶ አስፋው ሰለጠየቀ ድርቅ በጣም ያጠቃውን ሻይ  አቶ ማሞና ሌሎችም የእርሻ ትምህርት ተመራቂዎች  ለማሳየት ይዘውት ሄዱ። አቶ አስፋው ገና የመጀመሪያውን ቦታ ሲመለከት መጮህ ጀመረ። ተስፋ አስቆራጭ ነው ብሎ ተንገበገበ።አቶ ማሞ  ወደ ሌላው የሻይ ሁዳድ ጉዞውን አመራ። አቶ አስፋው የቁጣውን መጠን ከፍ አድርጎ እጆቹን እያወናጨፈ ራሱን እየነቀነቀ ወደ ቢሮ መልሱኝ ብሎ ፣ከዋናው መሥሪያ ቤት ለሚያገናኘው ራዲዮ የሚሆን መልዕክት ማርቀቅ ጀመረ።

EthioLion.Com

-፳-

„ከዋናው ሥራ አስኪያጅ በተሰጠኝ ትዕዛዝ የጉመሮን ሻይ ልማት ተዘዋውሬ ጉብኝቼ የጉመሮ ሻይ ተክል በተፈጠረው ድርቅና በአስተዳደር ጉድለት ዘጠና አምስት በመቶ መጥፋቱን ተገንዝቤአለሁ። ሙሉውን ሪፖርት በሚቀጥለው ሳምንት በጽሁፍ አቀርባለሁ“።

የሚል ሪፖርት ለዋናው መሥሪያ ቤት አስተላለፈ።

ጉመሮ በአዲሱ ዜና መበጥበጥ ያዘች። አይመሽም የለ ቀኑ መሸ የገብረመድህን ውሻ ይጮኻል። የጥላሁን ድመትም ከውሻው ትጣላለች።እንቁራሪቶቹና ፌንጣዎቹም የሰቆቃ ድምፃቸውን ያሰማሉ። የእሮብ ገበያ ጠጅ ቤትም እንደገና ሞላች። ሊቁና ገረመው ቦታቸውን ያዙ። አባ እሸቱም ፊታቸው ጠቁሮ በአንድ ጊዜ እርጅናው ያንሳቆላቸው መስለው ከመሃል ተቀመጡ። ግን ሁሉም አዲሱን ወሬውን ለመጀመር ፈሩ።

ይቀጥላል
በልጅግ አሊ

ሃሳብና አስተያየት ካሎት በሚቀጥለው ኢሜል ይጠቀሙ።

beljigali@beljigali.com

EthioLion.Com